**ሳምንታዊ ዜና (ሰኔ 28 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**10 ሺህ ማንበብና መፃፍ የማይችሉ የፌደራል ፖሊስ ምልምሎች ሁርሶ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ገቡ፣ የወያኔ ካድሬዎችም ለ1 ወር የደህንነት ኮርስ ጠላይ ሊገቡ ነው፣ ህዝቡ በርሃብ እያለቀ ቢሆንም ለዚሁ ኮርስ በቀን ብዙ ሺህ ብር ተመድቦላቸዋል፣ ሁለት አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የወያኔን የመያድ ረቂቅ አወገዙ፣ አፋኙና ጨቋኙ የፕሬስ ሕግ ፀደቀ፣ በእንቅልፍና በማጨብጨብ የሚያሳልፈው የወያኔ ምክር ቤት ተዘጋ፣ ነዳጅ እጥረት በሐገሪቱ ተከሰተ፣ በሀገሪቱ የተፈጠረው የዋጋግሽበት ወያኔ ያመጣው መሆኑ ተጋለጠ፣ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ኦዲተር መስሪያ ቤቱ ባቀረበው ሪፖርት በመናደድ ባለሥልጣናቱን አጉራ ዘለል ሲል ዘለፋቸው፣ ሕዝብ በሀረብና በኑሮ ውድነት እያለቀ ለመከላከያ ከ4 ቢሊዮን ብር በላይ ተመደበ፣ ቴዲ አፍሮ ለሐምሌ 4 ቀን 2000 ዓ.ም ተቀጠረ** »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»

ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ

……………………………………………………………………………………………

የወያኔው ቡድን ከመላ ሀገሪቷ ሕዝቦችና ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ ጋር የማይፈታ ቅራኔ ውስጥ ከገባ ጊዜ ጀምሮ ስልጣኑን በወታደራዊ ኃይል እያጠናከረ ለመቀጠል በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከፍተኛ የሀገር ሀብት እያባከነ መሆኑን ከተለያዩ መንግስታዊ ተቋም የሚደርሱን ጥቆማዎች ገለፁ ::

ለሀገርና ለሕዝብ ቅንጣት ታክል ግድ የሌለው ይኸው ቡድን ከዚህ ቀደም ከ400 ሺህ በላይ ወታደሮችና ፌዴራል ፖሊሶችን አሰልጥኖ በስራ ላይ አሰማርቶ ያለ ቢሆንም አሁንም በፍርሀትና በስጋት ውስጥ ያለ በመሆኑ በድጋሚ ሰሞኑን ከተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች ለፍዴራል ፖሊስነት መልምሎ ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ማስገባቱ ታውቋል::

ከ10 ሺህ በላይ ወደ ሁርሶ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ተቋም የገቡት እነኚሁ አዲስ ምልምል የፌዴራል ፖሊስ አባሎች ሲሆኑ፤ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተመልምለው ሰኔ 20 ቀን 2000 ዓ.ም ወደ ማሰልጠኛው የገቡ ሲሆን፣ በአሁን ሰዓት ሕዝቡ ምግብ እየጠየቀ ባለበት በዚህ ወቅት ህዝብን ጉዳይ የሆኑትን አስመርቆ ለማውጣት መጣደፉ የሚያሳዝን መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል::

የወያኔ ቡድን ከዕለት ወደ ዕለት የሕዝቦችንን እልቂት በተለያየ መንገድ እያስፋፋ ያለ ሰይጣናዊ ቡድን መሆኑ ቀድሞ የታወቀ ነው ያሉት አንድ የአዲስ አበባ ነዋሪ እኛ ለእለት ጉርስ የምንቀምሰው አጥተን በተቸገርንበት በዚህ ወቅት ወቅት ሕዝቡ ፍራቻና ጥላቻ ወስጡ ስላለው ብቻ በብዙ መቶ ሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ ውጪ አድርጐ ለማሰልጠንና መልሶም የሕዝቡን አንደበት ለመሸበብ መሯሯጡ የቡድኑን ማንነት ያጋለጠ ነው ሲሉ ገልፀዋል::

የኑሮ ወድነቱ እጅግ እየናረ የአለም አቀፉ ተቋማት እንኩዋን በኢትዮጵያ የተከሰተው ችግር ከሌሎች ሀገራት የተለየና አጣዳፊ እርዳታ የሚያስፈልግ ነው በማለት እየወተወቱ ባለበት ወቅት የወያኔ ቡድን ስልጣኔን ይጠብቁልኛል በሚል ብቻ ያልተማሩትን ዜጐች ከገጠር እየመለመለ ወደ ሁርሶ ማሰልጠኛ መውሰዱ ይበልጥ ያንገበግባል ያሉት እኚሁ አባት ከረሀቡ በላይ በቁማችን የገደለን ሳያንሰው እንዳንተነፍስ አንደበታችንን ሊለጉመው መጣደፉ የሚያሰዝን ነው ሲሉም ገልፀዋል::

በወር 700 ብር ደሞዝ፣ የቤት፣ የምግብ፣ የልብስ፣ የሕክምና ወጪ መንግስት ይችላችኋል ተብለው ማንበብና መፃፍ እንዲሁመ ምንም ማገናዘብ የማይችሉን ከገጠር ውስጥ መልምሎ ያመጣቸው ሲሆን፣ ይህም የተደረገው የታዘዙትን ሁሉ በድፍረት እንዲፈፅሙ መሆኑን የወታደራዊ ባለሙያዎች ይገልፃሉ::

ከ3 ወር ወዲህ 10 ሺህ የፌዴራል ፖሊሶችን በሁርሶ ማሰልጠኛ አሰልጥኖ ያስመረቀ ሲሆን፣5ሺህ ያህሉን በአዲስ አበባ የተቀሩትን በሌሎች ከተሞች ያሰማራ መሆኑን የገለፁት የፌዴራል ፖሊስ ምንጮች አሁንም 10ሺህ ምልምሎች ሁርሶ ማሰልጥኛ ያስገባ መሆኑን አረጋግጠዋል::

*ሀገሪቷ ሕዝቦቿን መቀለብ ያልቻለች ደሀ ነች እየተባለ በብዙ አለም አቀፍ ተቋማት ዘንድ ከፍተኛ ስጋት ያሳዳረ ቢሆንም የወያኔው ቡድን ግን በየጊዜው በብድርና በእርዳታ የሚያገኘውን ገንዘብ ወታደራዊ ተቋም ለማስፋፍያ እያዋለው መሆኑን የገለፁት የፌዴራል ፖሊስ ምንጮች በየእስር ቤቱ ያሉት ዜጎች በምግብ እጦት እያረገፉ ባለበት ወቅት መፍትሄ መስጠት ተስኗቸው መልሰው አዲስ ምንም ያማያውቁ ያልተማሩትን አታልለው ወደ ማሰልጠኛ ማስገባታቸው ስርዓቱ ከፍተኛ ችግር ውስጥ መዘፈቁን ያመላከተ ነው ሲሉ ተችተዋል፡፡*

*ስህተትን በስህተት የሚያርመው ይኸው የወያኔ ቡድን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ ከ60 በላይ እስር ቤቶችን አቋቁሞ በእያንዳንዱ እስር ቤት ከ1000 በላይ እያጐረ የሚቀልበው አጥቶ እየተቸገረ ባለበት ወቅት እንኩዋን አዲስ ምልምል አምጥቶ ማስገባቱ የሚያሳዝንና በዜጎች ላይ እየቀለደ መሆኑን ያሳያል ያሉት አንድ የኮማንደር ማዕረግ ያላቸው መኮንን ወያኔዎች የሚሰሩት ምን እንደሆነ ለማወቅ ገና ይቀረናል ሲሉም በጥርጣሬ ይገልፃሉ፡፡*

*በዝዋይ፣ በድሬዳዋ፣ በሸዋሮቢትና በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ያሉ ዜጎች የእለት ጉርስ አጥተው ተቸግረው ወትሮ የሚመገቡት የዘንጋዳ ቅልቅል እንጀራ ጠፍቶ በቀን ሁለት ጊዜ 5 በ11 በሚል ፊሊጥ የበቆሎ መጠኑ ያነሰ 2 ዳቦ እንደ ውሃ ከቀጠነ ሽሮ ጋር ብቻ እየተሰጣቸው መሆኑን ያጋለጡት የእስር ቤት ምንጮች ችግሩ በተለይም በዝዋይና በሸዋሮቢት ያየለ በመሆኑ በርካታ እስረኞች ለበሽታ እየተዳረጉ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡*

*በተንዳኝ የየእስር ቤቱ ሹማምንት በችግሩ ዙሪያ ለመነጋገር በሚል ከያሉበት አዲስ አበባ ተሰባስበው በአበልና በምግብ እራሳቸውን እያዝናኑ ከመሆኑም ባሻገር በስብሰባው መደምደሚያ ዕለት በውስኪና በጮማ ሲራጩ እንደነበር የተከታተሉ አንድ የማረማያ ቤት ኮሚሽን ሲቪል ሠራተኛ በዚህ በሚመነዝሩት ገንዘብ ለእስረኞች ቀለብ ቢገዛ ስንት ዜጐች ከጠኔ በዳኑ ነበር ግን ፈፅሞ ይህ ሊታሰባቸው የማይችል የጌቶቻቸው ቢጤ ልበ ድፍን ናቸው ሲሉ በሀዘን ተውጠው ገልፀዋል፡፡*

*ዜጐች እንደቅጠል እየረገፉ ባለበትና የወታደራዊ ተቋሙን በማጠናከር ላይ ባለበት ወቅት ሰሞኑን የኦህዴድ የተባለው የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት ካድሬዎቹን ለተሃድሶ በሚል ወደ ጦላይ ማሰልጠኛ ሊያስገባ መሆኑ ተጋለጠ፡፡*

*ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ነሐሴ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ለአንድ ወር የሚቆየው ይኸው ተሀድሶ ተብዬ ስልጠና ስርዓቱ እየተንገዳገደ ባለበት በዚህ ወቅት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን የገለፁት ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች በየቀኑ ከፍተኛ አበል የሚከፈላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ የምግብና የመኝታ ወጪም ከሕዝብ ካዝና እንደተመደበላቸው አጋልጠዋል፡፡*

*በተለይ የኦህዴድ ካድሬዎች ብቻ የሚሳተፉበት ይኸው ለ1 ወር የሚቆየው ስልጠና በጦላይ ውስጥ የሚደረግ ሲሆን በአሁን ሰዓት በኦሮሚያና በተቀሩትም የሀገሪቷ ክፍሎች ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰበት ያለው ወያኔ በመደንገጡ ካድሬዎቹን የደህንነት ስራ ሁሉ እንዲሰሩ ለማድረግ ስልጠናው እንደተዘጋጀ ገልፀው ለህዝብና ለወገን አንዳችም ርህራሄ የሌለው በመሆኑ እንጂ በሀረር፣ በባሌ፣ በአርሲ እና በተቀሩትም የሀገሪቱ ክፍሎች ዜጐች በረሀብና በኑሮ ወድነት እያለቁ ይህን ከፍተኛ ወጪ አድርጐ ማሰልጠን ተገቢ አይደለም ያሉት አንድ የወለጋ ነዋሪ በዚህ አይነት መንገድ ስልጣን ለማራዘም መሞከር ፈፅሞ ስህተት ነው ሲሉም ይተቻሉ፡፡*

*በቆሎ ከ600 ብር በላይ ባናጠረበት በዚህ ወቅት በቀን በሺህዎች የሚቆጠር ገንዘብ ወጪ አድርጐ ካድሬዎቹን ማሰልጠን ለህዝብና ለወገን የማያስቡ አእምሮ ያልፈጠረባቸው ስግብግብ ግለሰቦች የተጠራቀሙበት ቡድን መሆኑን በግልፅ ያሳያል ብለዋል፡፡*

በኢትዮጵያ ውስጥ ሲንቀሳቀሱ የቆዩት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የወያኔ ቡድን ለመዝጋት ሲል አፋኝና ገዳቢ ረቂቅ ሕግ ማውጣቱን ሁለት አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ተቃወሙ::

ሰሞኑን በወያኔ ተረቅቆ ሊፀድቅ እየተንደረደረ ያለውን ሕግ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂዮማን ራይትስዎች የተባሉት ሁለት ታዋቂ አለም አቀፍ ድርጅቶች በፅኑ የኮነኑ ሲሆን በሀገሪቷ ውስጥ ሠላም፣ ዲሞክራሲ፣ በአስተዳደርና በሌሎችም መንገዶች እገዛ እንዳያደርጉ የሚገድብ በመሆኑ ሊታሰብበት ይገባል ሲሉም ኮንነዋል::

ወያኔ የራሱ ጥላ እያስበረገገው በአንድ ጀንበር ህግ አርቅቆና አፅድቆ ተግባራዊ እያደረገ ባለበት በዚህ ወቅት የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ተግባርና ሚና ለማሳነስና ብሎም ለማባረር አስቦ ያወጣው ሕግ መሆኑን የገለፁት አንድ የአለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅት ሠራተኛ በ1997 ዓ.ም የታየውን ሁኔታ በመፍራት የተረቀቀ መሆኑ በግልፅ ያሳያል ብለዋል::

አሁን የተረቀቀው ሕግ በፍፁም የማያሰራና ገዳቢ ነው ያሉት ሁለቱ አለም አቀፍ ድርጅቶች በዲሞክራሲ ግንባታው ላይ ክፉኛ ጫና የሚፈጥር በመሆኑ ሊነሳ ይገባል ሲሉም አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል::

እነዚህ ለሰብአዊ መብቶች መከበር የቆሙ አለም አቀፍ ድርጅቶች ወያኔ ያወጣውን ረቂቅ ከሚቃወማቸው በለይ አፋኝና ገዳቢ ነው ሲሉም ኮንነዋል::

የሚሰራው ሥራ እያስበረገገው ያለው የወያኔው ቡድን ሁሉንም መንቀሳቀሻ መንገዶች ክርችም አድርጐ ዘግቶ ድርጅቶቹን አላሰራ ለማለት የጀመረው አሁን ባይሆንም የአሁኑ ግን በሀገሪቷ ውስጥ አንዳችም ለጋሽ ድርጅቶች እንዳይኖር ለማድረግ አስቦ መሆኑን የገለፁት የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት ሠራተኞች ይብዛም ይነስም ለህዝቡ መንግስት ነኝ ከሚለው ወገን በተሻለ መልኩ ጥቅም የሚሰጡ መሆናቸውን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል ሲሉ ገልፀዋል::

የሀገሪቷ ሕዝቦች በረሀብ አለንጋ እየተገረፉ ባለበት ወቅት አፍኖ ማንም እንዳይሰማ ሲያደርግ የቆየውን ወያኔን ገመና እነዚሁ አለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ያጋለጡ መሆናቸውን የገለፁት ሠራተኞች በተለይም የወያኔው አምባገነናዊ አካሄድን ሁሉ በመቃወም ለአለም ህዝብ እያጋለጡ በመሆናቸው ይህንን ሁሉ ተግባር እንዳያከናውኑ ለማድረግ ታስቦ የተረቀቀ ህግ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል::

በ1997 ዓ.ም በሀገሪቱ በተደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሲያበረክቱ የነበሩት እነዚሁ ለጋሽ ድርጅቶች በወቅቱ ወያኔ በቁሙ ሞቶ ሊቀበር እንደነበር ያስታወሱት አንድ የመያድ ሠራተኛ ያችን ጊዜ ቁጭቱን ለመወጣትና ዳግም የ1997 ሁኔታ እንዳይከሰት ለማድረግ ሲባል ፍራቻውን በረቂቅ ሕጉ ላይ ቁልጭ አድርጐ አስቀምጦታል ብለዋል:::

አክለውም በዚሁ ረቂቅ ላይ ለመወያየት ከወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ጋር የተገናኘን ቢሆንም የተረቀቀው ሕግ እንደማይሻሻል ጠረጴዛውን በቡጢ እየነረተ እያስፈራራ ነግሮናል ያሉት እኚሁ ሠራተኛ በወቅቱ ጊዜ ይስጠንና እንወያይ ብለን ብንጠይቅም ኤምባሲ ሄዳችሁ ልትማፀኑ ነው ለነገሩ ሄዳችሁም ቀራችሁም ይሄ ሕግ ከመፅደቅ የሚያግደው የለም:: ደግሞ በኛ ስራ ማንም አያገባውም እያለ እንደ ሰፈር ውስጥ ጐረምሳ ሲወናጨፍ መዋሉን አብራርተዋል::

ወያኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሕዝቡ ላይ እየፈፀመ ያለው ዘግናኝ ተግባር እየሰፋና እያደገ በመሄዱ የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም እንዲሉ በሁሉም መስኮች ሕግ እያወጣ ሕዝቡን አፍኖ ለመግዛት ካለው ሕልም የመነጨ እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም ለጊዜው ለመሄድ ቢችልም ግን ውጤታማ አይደለም ያሉት ሌላው የሕግ ባለሙያ የተረቀቀው ህግ ፍፁም የማያሰራ በሀገራችን ለጋሽ ድርጅት የሚባል እንዳይኖር የሚያደርግ ነው ብለዋል::

ከ10 በመቶ በላይ ገንዘብ ውጭ የሚያገኝ ከሆነ የአለም አቀፍ ድርጅት በመሆን መመዝገብ አለበት በማለት መለስ ዜናዊ እያስፈራራ የገለፃላቸው አስገራሚ ነው ያሉት እኚሁ የሕግ ባለሙያ እንኳዋን ድርጅቱ

የሀገሪቷ አመታዊ በጀት ከውጭ በተገኘ ገንዘብ መሆኑን እያወቀ ይህንን የመሰለ አሳፋሪና የሻገተ ሀሳብ ማቅረቡ ይገርማል ሲሉም ገልፀዋል፡፡

አሁን ያለውን ሕግ ለማሻሻል የበለጠ ግልፅነት ለማላበስ ነው እያለ የወያኔ ቡድን ስለ ረቂቁ ቢናገርም አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ግን ህጉ አያሰራም ገዳቢ ነው እያሉ እያወገዙት ይገኛል፡፡

ወያኔ በሚፈፅመው ግፍ የተነሳ የራሱን ጥላ እያየ የሚደነብርበት ወቅት ላይ በመድረሱ የተነሳ በሁሉም መስኮች አፋኝና ጨቋኝ ህጐችን እያወጣ መገኘቱም የፍርሃቱ መገለጫ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ለብዙ ዓመታት ሲንከባለል የነበረው የፕሬስ ሕግ ሰሞኑን በወያኔ ም/ቤት ተብየው የፀደቀ መሆኑ ታውቋል፡፡ አፋኝ፣ ገዳቢ እና ጨቋኝን የፕሬስ ህግ በመቃወም አለም አቀፍ ድርጅቶች ተከታታይ መግለጫ ቢያወጡም በፍርሃት የደነበረው ወያኔ ግን በፍፁም አይሞክርም በማለት ማክሰኞ ሰኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም ማፅደቁ ታውቋል፡፡

ሳይጠሯቸው አቤት፣ ሳይልኩዋቸው ወዴት የሚሉት የወያኔ ሆድ አደር የምክር ቤት አባል ተብዬዎች በአንገታቸው ላይ ሰይፍ ተመዝዞ ያለ መሆኑ እንኩዋን እያወቁ ያለ አንዳች ተቃውሞ ጨቋኙን ሕግ ያፀደቁት ሲሆን፣ ጥቂት የተባሉ የተቃውሞ ፓርቲዎች ቢንጫጩም ምንም ውጤት ባለማምጣታቸው ህጉ የፀደቀ ሲሆን ከዚህ በኋላ በሃገሪቷ ውስጥ መንግስትን የሚተች እና የሕዝብን ብሶት የሚያጋልጥ ነፃ ፕሬስ ያከተመለት መሆኑን የገለፁት አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር አሁን ከጨለማ ወደ ድቅድቅ ጨለማ መግባታችን በግልፅ የታየ ነው ሲሉም በስጋት እና በፍርሃት ገልፀዋል፡፡

በቤተ መንግስት ዙሪያ ተሰብስበው የሚያውካኩት የወያኔ ባለሥልጣናት ነግ በእኔን የማያዩ ብቻ በመሆናቸው አፋኝና ጨቋኝ የፕሬስ ሕጉ እንዲፀድቅ ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርጉ የቆዩ መሆኑ የሚያሳፍር ነው ያሉት እኚሁ ምሁር ትላንት ስልጣን ላይ የነበሩት ዛሬ ወህኒ የወረዱትና የተባረሩት ባለሥልጣናት ችግር ደረሰብን ያሉትን ሀሳብ ሁሉ ሲያስተናግ የነበረው የነፃው ፕሬስ ውጤት መሆኑን በመዘንጋት ያሉትን በጣት የሚቆጠሩ የፕሬስ ውጤቶች ግብአተመሬታቸውን ማፋጠናቸው የወያኔ ባለሥልጣናት አዙሮ ማሰቢያ የሌላቸው መሆናቸውን በደንብ ያረጋገጠ ነው ሲሉም ይኮንኗቸዋል፡፡

እብሪት ለደርግም አላዋጣ ያሉት እኚሁ ምሁር የወያኔ ባለሥልጣናት ያለ እውቀታቸው ስልጣን ተሸክመው በአንድ ሰው ጭንቅላት እየተሽከረከሩ ሃገሪቷንና ሕዝቧን ከመቼውም ጊዜ በላይ ወደ አረንቋ የከተቷቸው መሆኑን በዚህ በፀደቀው በፕሬስ ህጉ መመልከት ይቻላል ሲሉም ገልፀዋል፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት ጥቂት የነፃ ፕሬስ ውጤቶች የነበሩ ቢሆንም ጋዜጠኞቹን አዋክበው ለእስርና ለስደት የዳረጓቸው ወያኔዎች ዛሬ ደግሞ የበለጠ በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሸምቀቆ ገመድ በአንገታቸው ላይ እንዳሰሩ ሊታወቅ ይገባል ሲሉም በርካታ ምሁራኖች በብስጭት ይገልፃሉ፡፡

በማጨብጨብና በማንቀላፋት ለአንድ ዓመት ያህል የዘለቀው የወያኔ ተወካዮች ምክር ቤት ተብዬ ስራውን አጠናቀቀ ተብሎ ተዘጋ፡፡

ከሰኔ 30 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት ወር መጀመሪያ ድረስ የሚዘጋው ይኸው ምክር ቤት ተብዬ አባሎቹ አንድም ቀን ሀሳባቸውን ሳይገልፁ እንደ አሸንጉሊት ተቀምጠው በማጨብጨብ አሊያም በማንቀላፋታቸው ብቻ ከሀገሪቷ ሕዝቦች የተሰበሰበውን ገንዘብ ሰያኙኩት የቆዩ ሲሆን አሁን ደግሞ በክረምት ወደ ተመረጡበት ቦታ ሄደው እንዲመለሱ ብቻ ለእያንዳንዱ የወያኔ ምክር ቤት አባል 3 ሺህ ብር እንደሚሰጣቸው ታውቋል፡፡

በሀገርና በህዝብ ላይ ወንጀል ሲፈፅም እያንቀላፉ የሚያጨበጭቡት እነዚሁ የምክር ቤት አባል ተብዬዎች በኤድስ ዙሪያ በተመረጡበት አካባቢ ሰርተው እንዲመጡ በሚል ሰበብ 3ሺህ ብር ለእያንዳንዳቸው የሚሰጣቸው

ሲሆን ህዝቡ ግን የዕለት ጉርሱን ለመሸፈን ተቸግሮ ያለበት ደረጃ ላይ መድረሱ የሚታወቅ ነው የሚሉት ምሁራኖች ምን እየተሰራ እንዳለ እንኩዋን የማይረዱ መሆናቸውን የስርዓቱ ዝቅጠትን ያመላከተ ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል በሀገሪቱ በተከሰተው የኑሮ ወድነት ሳቢያ በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች ከፍተኛ ችግር የተፈጠረ ሲሆን፣ በተለይ ሰሞኑን ነዳጅ ከአዲስ አበባ ውጭ የለም እየተባለ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ መሆኑን ከተለያየ አካባቢ የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

ወያኔ የሀገሪቷን ሀብት እየቸበቸበ ለወታደራዊ ተቋም ግንባታ እያዋለው በመሆኑ በሀገሪቷ ውስጥ የውጭ ምንዛሬ ጠፍቶ በርካታ ነጋዴዎች ከጨዋታ ውጭ ለመሆን የተደረጉ ሲሆን፣ ለነዳጅ መግዣ እንኩዋን የሚሆን የውጭ ገንዘብ በመጥፋቱ የተነሳ ነዳጅ እንደልብ ባለመግባቱ እጥረቱ ሊከሰት እንደቻለም የገለፁት የቶታል ካምፓኒ የውስጥ አዋቂ ምንጮች በዚሁ ከቀጠለ በጥቂት ቀናት ውስጥ ከፍተኛ ቀውስ ይፈጠራል ተብሎ እንደተሰጋም አጋልጠዋል፡፡

ከአዲስ አበባ 300 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ያሉ ከተሞች በአሁን ሰዓት ነዳጅ እንደልባቸው ካለማግኘታቸው ተነሳ በየአካባቢው የሚንቀሳቀሱ መኪናዎች ለመቆም የተገደዱ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆ የኑሮ ወድነቱም ከዚሁ ጋር ተያይዞ እየናረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ወያኔ በስልጣን ላይ ለመቆየት ሲል የሀገሪቷን አንጡራ ሀብት በሙሉ ለወታደራዊ ተቋም እያዋለው በመሆኑ ከውጭ የሚገባው ነዳጅና ሌሎችም መሠረታዊ ፍጆታቸውን ለመግዛት በመቸገሩ አሁን በተወሰነ መልኩ የተፈጠረው የነዳጅ እጥረት በቅርቡ የከፋ ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል ሲሉም የቶታል ካምፓኒ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ስጋታቸውን ይገልፃሉ፡፡

በሀገር ውስጥ ያሉትን ነጋዴዎች እንዳይንቀሳቀሱ የውጭ ምንዛሬ እየከለከሉ ለራሳቸው እድሜ ማራዘሚያ የጦር መሣሪያ በውድ ዋጋ ከመግዛ ቸውም በተጨማሪ በየግላቸው ከፍተኛ ገንዘብ በውጭ ሀገር እያከማቹ ነው ያሉት አንድ የኢኮኖሚ ባለሙያ ወያኔ ካዝናው ባዶ ሆኗል ቢከፍቱት ተልባ እንዲሉ ባዶውን እየጮኸ ህዝቡን ለማደናቆር ይከጅለዋል ሲሉ ተችተዋል፡፡

በሀገሪቷ ውስጥ በመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ከፍተኛ ገንዘብ ምዝበራና ብክነት መኖሩን የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በመግለፁ መለስን አስቆጣ፡፡

ኦዲተር መስሪያ ቤቱ የ2000 ዓ.ም በጀት በአግባቡ መከናወንና አለመከናወኑን ለተወካዮች ምክር ቤት ተብዬ ባቀረበው ሪፖርት ላይ ባጋለጠው መሠረት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ከፍተኛ የሕዘብ ገንዘብ እየመዘበሩ መሆኑን ገልፆ የተሰጣቸውን ገንዘብም በአግባቡ ሊጠቀሙበት እንዳልቻሉም አስረድቷል፡፡

የኦዲተር መስሪያ ቤቱ ይህንን ሪፖርት ያቀረበው የ2001 ዓ.ም በጀት ለማፅደቅ ያለፈው ዓመት በጀት እንዴት ተከናወነ? ለሚለው ምላሽ ለመስጠት ሲሆን ተቃዋሚ የፓርላማ አባላት ይህንኑ የኦዲተር መስሪያ ቤት ሪፖርት ካደመጡ በኋላ በርካታ ጥያቄዎች ያነሱ መሆኑም ታውቋል፡፡

በተለይም በሀገሪቱ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት እንዲፈጠር ያደረገው ወያኔ ከብሔራ ባንክ ሕጉ ከሚፈቅደው ውጭ ብር በመበደሩና ስራ ላይ በመዋሉ መሆኑን አፅንኦት ሰጥተው የገለፁት ተቃዋሚዎች አሁንም የተያዘው በጀት ድልድሉ ከፍተኛ ጉድለት ያለበት ነው ሲሉም ተችተዋል፡፡

በተለይም በአሁን ሰዓት በሀገሪቱ ከፍተኛ የኑሮ ውድነትና ረሀብ በተከሰተበት ወቅት ምንም አይነት እርምጃ ያልተወሰደ ነው ያሉት ተቃዋሚዎቹ ችግሩን ለመቅረፍ እርምጃ ካለመወሰዱ በተጨማሪ በበጀት ውስጥ እንኩዋን ምንም አለመባሉ የሚያሳዝን ነው ብለዋል፡፡

አክለውም ሀገሪቷ ከምትችለው በላይ ከ4 ቢሊዮን ብር በላይ ለመከላከያ መመደቡ እጅግ አስደንጋጭ ነው የሚሉት እነዚሁ ተቃዋሚዎች እየተወሰደ ያለው እርምጃና እየተደረገ ያለው ሁሉ እጅግ አሳዛኝና በሀገርና በሕዝብ መቀለድ ነው ሲሉ ወያኔን ወንጅለዋል::

በተቃሚዎቹ ጥያቄና ተቃውሞ እንዲሁም በዋና ኦዲተር መ/ቤት ሪፖርት የተበሳጨው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በዘንድሮው አመት ለመከላከያ የተያዘው በጀት በ500 ሚሊዮን ብር ከፍ ያለ መሆኑን ጠቅሶ ነገር ግን እጅግ በጣም ትንሽ ብር መሆኑን ገልጿል::

ባለሥልጣናት ከብሔራዊ ባንክ ተበድረው የወሰዱትን ገንዘብ አስመልክቶ ምንም እንደማያውቅ የገለፀው መለስ ይልቁንም ይህንን ድርጊት ፈፅመዋል የተባሉ ባለሥልጣናት ካሉ ተጣርቶ ለጥያቄ እንዲቀርቡ እናደርጋለን ካለ በኋላ አጉራ ዘለል እያለ መልሶ ሲያብጠለጥላቸው ተደምጧል::

የመለስን ምላሽ ያደመጡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር እንዳሉት ከሆነ የወያኔው መሪ ምንጊዜም ውሸት አያልቅበትም ዛሬ ምክር ቤት ውስጥ የራሱን ባለሥልጣናት አጉሮ ዘለል እያለ የሚያብጠለጥለው እሱ ሳያውቅ ያውም 3 ቢሊዮን ብር ከብሔራዊ ባንክ ተበድረዋል መባሉ ውሸት ነው:: እንኳዋን ይሄንን ያህል ገንዘብ ቀርቶ የመርፌ ታክል ቀዳዳ የሆኑ ክፍተቶችን ያውቃል:: ነገር ግን መካድና መዋሸት ያደገበትና የጉለመሰበት በመሆኑ ባለሥልጣናቱን ተጠያቂ ለማድረግና ለሀገርና ለወገን ተቆርቋሪ መስሎ ለመታየት ያደረገው ሙከራ ነው ብለዋል::

አያይዘውም የገሀገራቱ ሕዝብ በረሀብ እየሞተ መሆኑን እየተረዳ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ብቻ ለመከላከያ ከ4 ቢሊዮን ብር በላይ መመደቡና ይህም ያንሳል ማለቱ በእጅጉ የሚያሳፍር ነው ብለዋል::

ዛሬ ወያኔ በፈጠረው የዋጋ ግሽበት በአለም ላይ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት የተከሰተው በኢትዮጵያ ብቻ መሆኑን የገለፁት ምሁሩ የወያኔው መሪ መለስ እንደ እስስት ባህሪውን እየቀያየረ ለ17 ዓመታት የዘለቀ ሲሆን ይህንን ባህርይ አሁንም ማሳየቱ የሚያሳዝን ነው ሲሉ በብስጭት ይገልፃሉ::

በማያገባው እየገባ የሰብአዊና ቁሳዊ ኪሣራ እየደረሰበት ያለው ወያኔ ለመከላከያ የተመደበው በጀት አናሳ ነው የሚለው በሱማልያ ውስጥ ብቻ በቀየኑ የሚያወጣው ወጪ የትየለሌ ከመሆኑም በተጨማሪ በአሁን ሰዓት የወያኔ ጦር ከ400 ሺህ በላይ ሠራዊት እየቀለበ መሆኑም ይህም ቀላል ወጪ አይደለም:: ነገር ግን ሕዝብን ስለሚፈራ በጦር ብዛት ለመዝለቅ ያደረገው ነው ሲሉም ይወነጅላሉ::

የ2001 ዓ.ም በጀት 54.3 ቢሊዮን ብር የተመደበ ሲሆን ለጤናና ለትምህርት የተያዘው እጅግ አናሳ ነው:: ለመከላከያ፣ ለሀገርና ለደህንነትና መረጃ ግን ሀገሪቷ ከምትችለው በላይ ነው የተመደበው ይህ ከእርዳታና ከብድር ከሚያገኘው ገንዘብ ውጭ ነው እንጂ ያ ሁሉ ቢታሰብ የመከላከያ ዓመታዊ በጀቱ ከ10 ቢሊዮን ብር በላይ ሊያሻቅብ እንደሚችልም አንዳንድ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይገልፃሉ::

እውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) አርብ ሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም ፍርድ ቤት ቀርቦ ለሐምሌ 4 ቀን 2000 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶታል::

ለብይን ተብሎ የተሰጠው ቀጠሮ አቃቤ ሕግ ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ የቀን ልዩነት ያለው በመሆኑ ይህንኑ እንዲያስተካክል ለማድረግ ሲባል ተለዋጭ ቀጠሮ መሰጠቱ ይገርማል ያሉት አንድ የሕግ ባለሙያ ፍርድ ቤቱ የሚሄደው ጭፍን በሆነ መንገድ ነው እንጂ በቀረበለት ማስረጃ መሠረት መወሰን ነበረበት ብለዋል::

በዚህም ምክንያት በቀረበው የሰነድ ማስረጃ መሠረት መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ ይሰናበት ብሎ መወሰን ሲገባው የተሳሳተውን የአቃቤ ሕግ ማስረጃ አስተካክለህ አምጣ መባሉ በሕግ አግባብ የማያስኬድ መሆኑን የገለፁት እኚሁ ስማቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ የሕግ ባለሙያ የወያኔ ቁንጮ ሹም ልዑል ገብረ

ማርያም ግን የተሰጠውን ተልዕኮ ለማስፈፀም የተቀመጠ በመሆኑ ፍፁም አይን ያወጣ ፍርደ ገምድል የሆነ ስራ እየሰራ መሆኑ ያሳፍራል ሲሉ ገልፀዋል።

የቴዲ አፍሮ አድናቂና ቤተሰቦቹ ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ በፍርድ ቤት ሁለቱም መግቢያ በሮች ላይ ተሰልፈው የነበረ ሲሆን ቀድመው የደረሱት በሩ ሲከፈት ወደ ግቢ የገቡ ቢሆንም በችሎቱ የታደሙት እጅግ በጣም ጥቂቶች መሆናቸው ታውቋል።

እውቁ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ቀጠሮ ተሰጥቶት ሲወጣ እንደወትሮው ሁሉ ፊቱ ተከፍቶ እንደነበርና አድናቂዎቹና ቤተሰቦቹ በአንባ እየተራጩ ሲተቃቀፉ ተስተውሏል። ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ሰው ገጭተህ ገድለሃል በሚል ወያኔ ክስ ከመሰረተበትና ወህኒ ካወረደው በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ብይን ለመስጠት ለሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀጠሮ የተሰጠው ቢሆንም ተልካሻና ለፍስፍስ ምክንያት በመደርደር በድጋሚ ለመጨረሻ ጊዜ ብይን ለመስጠት በሚል ለሐምሌ 4 ቀን 2000 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶታል።

ሁለት ወር ከ19 ቀናት በባዶ ቤት ለእስር የተዳረገው ወጣቱ ዝነኛ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ጥቅምት 22 ቀን 1999 ዓ.ም ምሽት ላይ ደጉ የተባለው የጐዳና ተዳዳሪ ገድለህ ሸሽተል በሚል ሐሰተኛና የፈጠራ ክስ ወያኔ መስርቶበት እያሰቃየው ሲሆን የሰው ምስክር ተብለው የቀረቡት ምስክሮችም የሰጡት ቃል እርስ በእርስ የተጣረሰና የተቃረነ ሲሆንባቸው ሌላ የሰነድ ማስረጃ ቢያቀርቡም ይህ ማስረጃ የተምታታ በመሆኑ መፈናፈኛ ያጣው የወያኔው ካድሬ ዳኛ ልዑል ገብረ ማርያም መልሶ ሰነዱን ደልዞና ሰርዞ እንዲያመጣ ለአቃቤ ህግ ሲል የ7 ቀን ቀጠሮ መስጠቱ ታውቋል።